# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!






- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት:-
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)

<u>**መደበኛ ፕሮግራሞች**</u>

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

“እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ” ሉቃስ 2:10




“ሰው እንዲያይ እግዚአብሔር አያይምና ናቅሁት ፡ ሰው ፊትን ያያል ፡ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል “። (1ኛ ሳሙኤል 16:7)

| Chicago Yemsrach Evangelical Church<br>4455 N. Seeley Avenue<br>Chicago, IL 60625 | መደበኛ ፕሮግራሞች<br>እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.<br>አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m. |
|---|---|
| **August 18, 2019** | **ነሐሴ 12 ፤ 2011 ዓ.ም.** |

# የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት ........................... | ወንድም መኮንን ጂኔሎ |
| አምልኮ.......................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ ............ | እህት ሰናይት ከበደ |
| ቃል ............................... | ወንድም ብርሃኑ አንበሴ |
| ማጠቃለያ ..................... | ፕሮግራም መሪ |

## <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

"እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንኩት እርስዋንም እሻለሁ ፡ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውንም አይ ዘንድ ፡ መቅደሱንም እመለከት ዘንድ "። (መዳ 27፡4)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645 |
| ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ታብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም መስፍን ባፋ

## <u>የታዘዝነውን አናድርግ ፤ የተደረገልንን እናስታውስ</u>

"በሕይወት እንድትኖሩ እንድትበዙም እግዚአብሄርም ለአባቶቻችሁ ወደ ማለላቸው ምድር ገብታችሁ እንድትወርሱአት ዛሬ ለአንተ የማዝዘውን ትእዛዝ ሁሉ ታደርጉ ዘንድ ጠብቁ።" (ዘዳግም 8፤1)

"ትበላማለህ ትጠግብማለህ ስለተሰጠህም ስለመልካሚቱ ምድር አምላክህን እግዚአብሄርን ትባርካለህ።" (ዘዳግም 8፤10)

"ነገር ግን ዛሬ እንደ ሆነ ለአባቶችህ የማለውን ቃል ኪዳን ያጸና ዘንድ ፤ ሀብት ለማከማቸት እርሱ ጉልበት ሰጥቶሃልና አምላክህን እግዚአብሄርን አስብ።" (ዘዳግም 8፤18)

የዘዳግም መጽሐፍ ምዕራፍ ስምንትን በጥሞና ስናጠና ሁለት ዓብይት ጉዳዮችን እንመልከታለን። የመጀመሪያ አስርት ቁጥሮች፤ ነገሮች ወይንም ሁኔታዎች በከበዱ፤ የምንጨበጠውን የምንይዘውን ባጣን ፤ ማምለጫ ቀዳዳ የጠፋ በመሰለን ጊዜ በአጠቃላይ በምድረ በዳ ሳለን እግዚአብሄር ያደረገልንን እንድናስብ ፡ እንድናስተውል ያሳስቡናል። (ዘዳግም 8፤2) በዚሁ ክፍል ያሉት ቀሪዎቹ አስርት ቁጥሮች ደግሞ ነገሮቻችን አልጋ ባልጋ በሆኑልን፤በተመቹን፤ህልሞቻችን በተፈቱልን ፤ ቡቃያዎቻችን ጎምርቶ ፍሬ ባፈራልን ጊዜ ፈጠሪያችን እንድናስብ ያሳስቡናል ። (ዘዳግም 8፤16) ስለዚህ ይህ ምዕራፍ በአጠቃላይ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እያለን ፈጣሪያችንን እግዚአብሔርን እንድናስታውስ ፤ እንድንዘክር ፤እንድንባርክ አስረግጦ ያሳስበናል።

የሰው ባህሪይ ሆኖ አብዛኛዎቻችን መልካም በሆነልን ጊዜ የምስጋና ነዶ እናቅርባለን። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሳችን በማንኛውም ሰዓት በክረምት ሆነ በበጋ፤በማትረፍ ሆነ በመክሰር በማፍራት ሆነ በመጠውለግ፤ በማግኘትም ሆነ በማጣት ወቅት እግዚአብሄርን እንድናስብ ያሳስበናል ። በ2ኛ ዜና መዋዕል ምዕራፍ 20 ውስጥ የተጻፈውን ንጉስ ኢዮሳፍጥና የይሁዳ ሕዝብ ያጋጠመውን ፈተና ስንመለከትና የተወጣበትን መንገድ ስንረዳ ይህንኑ እንማራለን።

ኢዮሳፍጥ እጅግ በሚያስፈራ መልኩ ሞዓባውያን ፤ አሞናውያንና ምዑናውያን ሊወሩትና ሊወጉት ከየአቅጣጫው በተነሱ ጊዜ እግዚአብሄርን ለመፈለግ ፊቱን አቀናም ፤ ህዝቡንም በአንድነት በመሰብሰብ በእየሩሳሌም ጾምም አወጀ። ( 2ኛ ዜና መዋዕል ምዕራፍ 3-5) በጉባኤ መካከልም ለአምላኩ እግዚአብሄር እውቅና ሰጠ ፤ ሐይልና ሰልጣን የእርሱ የእግዚአብሄር እንደሆነም ተናገረ ፤ ለአብርሃም ዘሮች የገባውን በማስታወስ በፊቱ በመቆም ወደ እርሱም ጩሆም ፤ እንደሚሰማቸውና እንደሚያድናቸው መሰከረ ። እግዚአሄርም ሰምቶ በእሳት የሚመልስ አምላክ ነውና ንጉስና ሕዝቡን ታደጋቸውም አዳናቸውም ። በዚህ ሂደት ውስጥም እግዚአብሄር ህዝቡን ያስተምራል ያዘጋጃል። (2ኛ ዜና መዋዕል ቁጥር 6-8)።

ጌታ የተባረከ ይሁን። ይቀጥላል